# በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ለዳኞች እና ለህግ ባለሙያዎች የተዘጋጀ የካፒታል ገበያ ህጎች ማብራሪያ መጽሐፍ

## መግቢያ

ይህጽሁፍ የሪፖርት አይነት ይዘት ያለው ሲሆን በኢትዮጵያየካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት እና በኤፍ.ኤስ.ዲ ኢትዮጵያ (FSD) በሚባል ድርጅት ትብብር ተዘጋጅቶ ስለቀረበው የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ማብራሪያ መጽሐፍ ላይ የተካሄደውን የባለድርሻ አካላት ምክክር አጠቃላይ ትንተና ያቀርባል። መጽሐፉ በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ውስጥ ያሉ የህግ ማዕቀፎች እና ምርጥ አለም አቀፍ የካፒታል ገበያ ተሞክሮዎችን በመዳሰስ በተለይ ዳኞችእና የህግ ባለሙያዎች የካፒታል ገበያ አለመግባባቶችን በመፍታት ሂደት፣ኢንቨስተሮችን የመጠበቅ እና የገበያ ተዓማኒነትን ለማሳደግ ሊኖራቸው ስለሚችል ሚና ምን መሆን እንዳለበት የሚተነትንና እንደ ማጠቀሻ የሚያገለግል ነው።

የምክክር ሂደቱበኢትዮጵያ የሕግ እና የፋይናንስ ዘርፎች ውስጥ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን አሳትፏል። ከእነዚህም ውስጥ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ከፍትህ ሚኒስቴር ዓቃብያነ ህግ፣ ከፌዴራል ጠበቆች ማህበር የህግ ባለሙያዎች፣ ከካፒታል ገበያ ባለስልጣን፣ ከኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ (ESX) ፣ ከአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት፣ ከኢትዮጵያ የማስማማትና የግልግል ዳኝነት ማዕከል፣ ከካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች፣ የፋይናንስ ተቋማት እና የአካዳሚክ ባለሙያዎች ይገኙበታል።

የባለድርሻ አካላቱ ለመጽሐፉ አጠቃላይአቀራረብ እና ለተግባራዊ ጠቀሜታው ከፍተኛ ድጋፍ ያሳዩ ሲሆን የካፒታል ገበያ ተቋማትን ማንነት፣ በህግ የተሰጣቸውን ስልጣን፣ በካፒታል ገበያ የተከለከሉ የግብይት ተግባራትን ዝርዝር ትንተና እና ጠንካራ የኢንቨስተሮች ጥበቃአስፈላጊነትን በተመለከተ ውይይት ተደርጓል። በተለይ የካፒታል ገበያ የክርክር አፈታትን በተመለከተ ከቁጥጥር ሥርዓት እድገቶች ጋር ተዛማጅነትን ለመጠበቅ ሂደቱን ማቀላጠፍ እና ማዘመን እንደሚያስፈልግ ተጠቁሟል።

ይህሪፖርት የባለድርሻ አካላቱን የምክክር ሂደት በመተንተን ከባለድርሻአካላት የተሰጠውን ግብረ መልስ እና የተሰጡ ምላሾችን እንዲሁም የተደረጉ ማሻሻያዎችን ይዘረዝራል።

## የምክክሩ ዳራ እና አውድ

ኢትዮጵያ የተማከለ የካፒታል ገበያ ማዕቀፍ በመዘርጋት በኢኮኖሚ ልማቷ ውስጥ በለውጥ ሂደት ላይ ትገኛለች። የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 ለዚህ አዲስ ሥነ-ምህዳር የሕግ መሠረት የጣለ ሲሆን የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ሥራ መጀመር እና የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ፈቃድ ማግኘትን ተከትሎ ገበያው ሥራ በመጀመሩ በተለያዩ ፈቃድ የተሰጣቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች አማካኝነት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት እየተደረገ ይገኛል ።

የኢትዮጵያየካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤትም በባለሥልጣኑ በሚሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ይግባኞችን ለመስማት እና ከካፒታል ገበያ ግብይቶች የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት ልዩ የዳኝነት አካል ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 64 መሰረት ተቋቁሟል። የዚህአዲስ የካፒታል ገበያ ስኬታማነት የካፒታል ገበያ ጉዳዮችን በሚመረምሩ ዳኞች እና የገበያ ተሳታፊዎችን የሚያማክሩ ጠበቆች፣ ውስብስብ

የፋይናንስ መሳሪያዎችን የሚያማክሩ የኢንቨስትመንት አማካሪዎች፣ የቁጥጥር ማዕቀፎችን እና ልዩ የክርክር አፈታት ዘዴዎችን የመረዳት አቅም ላይ የተመሰረተ ነው። የካፒታል ገበያ ህጎች ማብራሪያ መጽሀፍ ማዘጋጀት ያስፈለገበት ምክንያትም በዳኞች እና በህግባለሙያዎች ዘንድ ተቀራራቢ የሆነ አረዳድ እና አተረጓጎም እንዲኖር ለማስቻል ነው።

## የመጽሐፉ ዓላማ

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ማብራሪያ መጽሐፍ ለዳኞች እና ለህግ ባለሙያዎች በርካታ እርስ በርስ የተያያዙ ዓላማዎችን ለማሳካት ያለመ ነው። በመጀመሪያ ለዳኞችና ለህግ ባለሙያዎች ስለ ካፒታል ገበያ ስራዎችና ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በተመለከተ ለውሳኔ አሰጣጥ እና የህግ ምክር አስፈላጊ የሆኑ የህግ እና የቁጥጥር እውቀትን ለማሳደግ ይረዳል። ሁለተኛ፣ መጽሐፉ በተለያዩ ክፍሎች እና ጉዳዮች ላይ የህግ ትርጓሜን ደረጃውን የጠበቀ ለማድረግ ያለመ ሲሆን፣ በካፒታል ገበያ ዳኝነት ውስጥ ተገማችነትን እና ወጥነትን ያበረታታል። ሶስተኛ፣ የህግ ባለሙያዎችን የካፒታል ገበያ ህጎችን በብቃት ለማስፈጸም፣ የማጭበርበር ባህሪን ለመግታት እና የኢንቨስተሮችን ጥበቃ ለማጠናከር እንዲሁም አራተኛ፣

አለመግባባቶችን በፍትሃዊነት እና በብቃት ለመፍታት የሚችል ጥሩ የሚሰራ የህግ ስርዓት በማሳየት፣ የመጽሐፉ በሀገር ውስጥ እና በውጪ ኢንቨስተሮች መካከል የገበያ ታዓማኒነትን ለማስጠበቅ ነው። በመጨረሻም፣ መጽሐፉ ለህግ ባለሙያዎችና ለዳኝነት ስልጠና ፕሮግራሞች እና በካፒታል ገበያዎች ላይ ያተኮሩ ቀጣይ የህግ ትምህርት መሰረታዊ ጽሑፍ ሆኖ ያገለግላል።

## የመጽሐፉ አወቃቀር

ለውይይት የቀረበውመጽሐፍ ባጠቃላይ ዘጠኝ ምዕራፎችን ይዟል። የመክፈቻ ምዕራፉ መሰረታዊ የካፒታል ገበያ ፅንሰ ሀሳቦችን ያስተዋውቃል፣ የካፒታል ገበያዎችን ኢኮኖሚያዊ ሚና እና በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ያብራራል።
በመጽሐፉ በመጀመሪያ ምዕራፍ፣ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ገበያዎች ያሉ መሆኑን፣ በመጀመሪያ ደረጃ ገበያ አውጪው በሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹን ለመጀመሪያ ጊዜ ለመሸጥ የሚያቀርብበት ሂደት መሆኑን እና ግብይቱ በአውጭውና ይህንን ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ለመጀመሪያ ጊዜ በሚገዛው ኢንቨስተር መካከል የሚደረግ ግብይት መሆኑን፣ሁለተኛ ደረጃ ገበያ ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ ገበያ ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣውን አዲሱን ሰነደ ሙዓለ ንዋይ በገዛው ኢንቨስተር እና ከሱ ለመግዛት በሚፈልጉ ሶስተኛ ወገኖች መካከል የሚደረግ ግብይት መሆኑን ያብራራል።

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድቤት

# በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ለዳኞች እና ለህግ ባለሙያዎች የተዘጋጀ የካፒታል ገበያ ህጎች ማብራሪያ መጽሐፍ

በምዕራፍ ሁለት የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ መሠረተ ልማት ዋና መሠረት የሆኑትን አራት ቁልፍ ተቋማት ይመረምራል። እነሱም የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ፣ ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤት እና የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ናቸው።

ምዕራፍሶስት ከሁሉም ዓይነት ኢንቨስተሮች እስከ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪዎችና ፈቃድ ያላቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ድረስ የካፒታል ገበያ ተዋንያንን በተመለከተ የሚተነትን ሲሆን ምዕራፍ አራት በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያዎች ውስጥ ሊገበያዩ የሚችሉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን፣ የዕዳ ሰነዶችን፣ ተዛማጅ ውሎችን ምንነት፣ የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንዶችን፣ የሸርዓ ህግን የተከተሉ የፋይናንስ ሰነዶችን እና አዳዲስ የካፒታል ገበያ መሳሪያዎችን ጨምሮ ይዘረዝራል።

ምዕራፍአምስት በተለይ በጋራ የኢንቨስትመንት ፈንዶች ላይ በማተኮር በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የሚገበያዩ የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንዶችን እና አማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንዶችን ይመረምራል። ምዕራፍ ስድስት በተቆጣጣሪ ማዕቀፍ ውስጥ የተካተቱትን የኢንቨስተር ጥበቃ ዘዴዎችን ይተነትናል።

ምዕራፍሰባት ስለ ካፒታል ገበያ የቁጥጥር ማዕቀፍ አጠቃላይ ትንተና ይሰጣል፣ የካፒታል ገበያ አዋጅን እና ሁሉንም የአፈፃፀም መመሪያዎችን ይመረምራል። ምዕራፍ ስምንት የተከለከሉ የግብይት ተግባራትን በአለም አቀፍ ማሳያ ጉዳዮች ታግዞ የሚያብራራ ሲሆን ለእያንዳንዱ ጥፋት ግልጽ የሆኑ ቅጣቶች ያላቸው መሆኑን ያስረዳል። የመጨረሻው ምዕራፍ የሕግ ባለሙያዎች የገበያ ተዓማኒነትን በማረጋገጥ ረገድ ያላቸውን ወሳኝ ሚና ይገልጻል።

## የውይይት ማዕቀፍ

የምክክሩ ሂደትየተነደፈው ከሁሉም ባለድርሻ አካላት አጠቃላይ ግብረመልስ ለመሰብሰብ በቂ ጊዜ እንዲሰጥ የሚያስችል መልኩ ሲሆን ከጥር ወር 2018 ጀምሮ ለአንድ ወር ጊዜ የመጽሐፉን ረቂቅ በአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ድህረ-ገጽ ላይ በማስቀመጥ ባለድርሻ አካላት እንዲያገኙት እና ቀድመው አስተያየታቸውን እንዲልኩ ተደርጓል።

በምዕራፍአንድ የካፒታል ገበያ ፅንሰ-ሀሳቦችን ውስን የፋይናንስ ዳራ ላላቸው አንባቢ የህግ ባለሙያዎች ተደራሽ የሚያደርግ ነው። በተለይ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ገበያዎች እንዴት እንደሚሠሩ ለህግ ባለሙያዎች ግልጽ ማብራሪያዎችን ተሰጥቶባቸዋል።

ምዕራፍሁለት ስለ አራቱ ቁልፍ ተቋማትና በካፒታል ገበያ ስነ ምህዳር ውስጥ ስላላቸው ሚናግልጽ በሆነ ማብራሪያ ይሰጣል። የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ሚና እና የዳኝነት ስልጣን በተመለከተ በተለይ በአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ እና በግልግል ዳኝነት መካከል ስላለው ልዩነት ዝርዝር ውይይት ተደርጓል። የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ባለሥልጣኑ የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች ለምሳሌ ፈቃድ መከልከል፣ መሰረዝ፣ ማገድ፣ ሰነደ አለመመዝገብ፣ ከምዝገባ መሰረዝ፣ የካሳ ፈንድ ይገባኛል ጥያቄዎች እና ሌሎች መሰል አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በተመለከተ በይግባኝ የሚያይ ሲሆን የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ደግሞ በአባላቱ እና በኢንቨስተሮች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን የሚፈታበት የማስማማትና የግልግል ዳኝነት አሰራር አለው። ከዚህ በተጨማሪ ገበያው በክርክሩ ተሳታፊ ከሆነ ጉዳዩ በአዲስ አበባ የንግድ ምክር ቤት የግልግል ዳኝነት ኢንስቲቲውት ወይም በኢትዮጵያ የማስማማትና የግልግል ዳኝነት ማዕከል የሚታይ መሆኑ ተብራርቷል።

ምዕራፍሶስት ከመጽሐፉ ውስጥ በጣም ጠቃሚ ከሆኑት ክፍሎች ውስጥ እንደሆነ በተለይ የሕግባለሙያዎች ደንበኞችን ለማማከር የተለያዩ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ምድቦች መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት አስፈላጊ መሆኑን ገልፀዋል።

ምዕራፍሶስት ከመጽሐፉ ውስጥ በጣም ጠቃሚ ከሆኑት ክፍሎች ውስጥ እንደሆነ በተለይ የሕግባለሙያዎች ደንበኞችን ለማማከር የተለያዩ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ምድቦች መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት አስፈላጊ መሆኑን ገልፀዋል።

ምዕራፍአራት በጥልቀት እና በግልጽነት በተለይም እስላማዊ የፋይናንስ መሳሪያዎችን ሽፋን የሚያደርግ ከመሆኑ ባሻገር ከእያንዳንዱ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አይነት ጋር በተያያዘ ሊኖር የሚችለውን የስጋት ሁኔታ ትንተና አካቷል።
ምዕራፍአምስት በረቂቅየጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ መመሪያ መሰረት በተለይ አካታች ኢኮኖሚን ከማረጋገጥ አንጻር ዝቅተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ሳይቀሩ በካፒታል ገበያ ሊሳተፉ የሚችሉበትን አግባብ በሚገባ ተብራርቶበታል።

ምዕራፍስድስት የካፒታል ገበያ ተቋማት ዋነኛ አላማ የሆነውን የኢንቨስተር ጥበቃ ዘዴዎች ላይ ያተኩራል። በአዋጁና መመሪያዎች ላይ ያሉ የኢንቨስተር ጥበቃ ዘዴዎች፣ በተለይ አውጪው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለህዝብ ከመሸጡ በፊት የደንበኛ ሳቢ መግለጫውን ፈቃድ ባለው አካል አሰርቶ በባለሥልጣኑ ማስፀደቅ እንደሚገባ፣ በቀጣይም በየጊዜው የፋይናንስ ሪፖርት ማቅረብ እንዳለበት፣ መሰረታዊ መረጃዎችን እና ለውጦችን ለህዝብ ይፋ ማድረግ እንደሚገባ በጥልቀት የተዳሰሱበት ምዕራፍ ነው። በግብይት ወቅት ለሚያጋጥሙ አለመግባባቶች አማራጭ የክርክር አፈታት ዘዴዎችና የካሳፈንድ አላማ ጉዳዮችም ትኩረት ተሰጥቷቸው በዝርዝር ተዳሰዋል።
ምዕራፍሰባት የካፒታል ገበያ አዋጅ እና መመሪያዎች ላይ ያሉ ዋና ዋና ነጥቦችን በሚመለከት ውስብስብ የሆነውን የአዋጅ እና የመመሪያዎቹን ድንጋጌዎች እና ከሌሎች ህጎች እና ልምዶች ጋር በማዋሃድ ይተነትናል። ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች መተዳደሪያ ደንቦች ላይ ማብራሪያ በመስጠት የህግ ባለሙያዎች ስለካፒታል ገበያ የህግ ማዕቀፍ አጠቃላይ ግንዛቤ ከአንድ ምንጭ እንዲያገኙ በሚያስችል ደረጃ ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

ምዕራፍስምንት በካፒታል ገበያ አዋጅ፣መመሪያዎች እና በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መተዳደሪያ ደንብ የተካተቱ የተከለከሉ የግብይት ተግባራትን በሌሎች ሀገራት ካፒታል ገበያዎች ከተፈጠሩ የህግ ጥሰቶችን በምሳሌነት በማንሳት እንዲሁም በምዕራፍ ዘጠኝም የህግ ባለሙያውን ሚና ግልጽ በሆነ መንገድ በመግለጽ መጽሐፉን በተግባር ስለመጠቀም አስፈላጊነት ውይይት ተደርጓል።
በውይይቱ የተገኙ የባለድርሻ አካላት አስተያየቶችን እንደ ግብዓት በመጠቀም በርካታ ተጨባጭ ክለሳዎች በመጨረሻው እትም ውስጥ ተካተዋል።

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድቤት

# በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ለዳኞች እና ለህግ ባለሙያዎች የተዘጋጀ የካፒታል ገበያ ህጎች ማብራሪያ መጽሐፍ

## ማጠቃለያ

ለዳኞችእና ለህግ ባለሙያዎች የተዘጋጀው የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ማብራሪያ መጽሐፍ ላይ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በተደረገው ውይይት ስለ መጽሀፉ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ከተሳታፊዎች በተነሱት ሃሳቦች በተለይም ለዳኞችና ባለሙያዎች የህጎችን አንድ ዓይነት ትርጓሜ ለማበረታታትና ውሳኔ ተገማችነት ለማረጋገጥ፣ እንዲሁም ለተቆጣጣሪዎችና ለካፒታል ገበያተሳታፊዎችን በካፒታል ገበያ ላይ የህግ ግንዛቤ ለማሳደግ፣ ተዓማኒነት ያለው የካፒታል ገበያ ስርዓት በሀገራችን ለመገንባት ከፍተኛ ጥቅም እንዳለውና በተጨማሪም መጽሐፉ እንደ ማጣቀሻና ለስልጠና ሰነድነት የሚያገለግል መሆኑ ተገልጿል።

የኢትዮጵያየካፒታል ገበያን ለማሳደግ ዳኞች እና የህግ ባለሙያዎች አለመግባባቶችን ለመፍታት፣ ኢንቨስተሮችን ለመጠበቅ እና ህጎችን ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን ልዩ እውቀት እንዲያገኙ ይህ መጽሐፍ ቀጥተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋል።